# የኛ ባለሙያ

(ከማህሌ በቀለ)

የራሷ አሮባት፣ የሰው ስታማስል
የጎረቤት ችግር፣ የምትፈታ ይመስል
የኛ ባለሙያ፣ የኛ እመቤት
ትቅርብኝ ትውጣልኝ፣ ትሂደው በእውነት!

በርሽ አይዘጋ፣ መስኮትሽ አይገጥም
ግድግዳሽ ልፍስፍስ፣ ጣርያሽ ያለ ጥምም
ወይ ንፋስ አይመክት፣ ወይ ዝናብ አያቆም
አንችም ባለቤት ነሽ፣ መቸም ወግ አይቀርም፡፡

የግንቦቱ ንፋስ፣ የሰኔው ዝናብ
ነጠላና ኩታ፣ በመከናነብ
በዋዛ አያልፍም፣ አስቢ ከልብ፡፡

ብርግድ ባለው በርሽ፣ የገባው ንፋስ
አልጋሽን ገልብጦ፣ ቤትሽን ሲያፈርስ
ሲኒዎች ሲንኳኩ፣ ሳህኖች ሲንቋቁ
አንሶላሽ ሲገለብ፣ ልብሶችሽ ሲወደቁ
ምንጣፍሽ ሲንፏቀቅ፣ ነፍስሽ ሲሽማቀቅ
ልክሽን አየነው፣ ሚስጥር አይደበቅ፡፡

ካንች በላይ ደግሞ፣ ፍርስርስ ባለ ቤት
ስትኖር የነበረች፣ ያንችዋ ጎረቤት
ከጌታሽ ጋር ገጥማ፣ የማይሆን ጦርነት
አሳዳሪ አጥታ፣ ስትቅበዘበዝ
ነገር ፈልጋኝ ነው፣ ሳይመጣ መዘዝ
ቀደም ብዬ ልምታት፣ ብለሽ እሮጠሽ
ገንዘብ ጥይት ስጠኝ፣ ብለሽ ለጌታሽ
ለማንም የማይበጅ፣ ችግር ውስጥ ገብተሽ
በገዛ ራስሽ ላይ፣ ጠላት አበዛሽ፡፡

ድስትሽን ያሳረረው፣ እሳቱ አይደለም
ድስትሽን ያሳረረው፣ እንጨቱ አይደለም
ድስትሽን ያሳረረው፣ ጉልቻው አይደለም

ድስትሽን ያሳረረው፤ ንፋሱም አይደለም
ድስትሽን ያሳረረው ማንም፤ የሚያውቀው ነው
የችሎታ መጥፋት፤ የሙያሽ ማነስ ነው፡፡

መማር ካስፈለገሽ፤ የቤት አያያዝ
መለየት እንድትችይ፤ መድሀኒት ከመርዝ
ታላላቅ ምሁራን፤ ወደሚገኙበት
ቃሊቲ ብትወርጂ፤ ወደአንችው እሥር ቤት
ሙያ ብቻ ሳይሆን፤ ፍቅር ትማርያለሽ
ይኸ ሐቅ መሆኑን፤ አንችም ታውቂዋለሽ፡፡

ቃሊቲ እሥር ቤት፤ አንች ያጎርሻቸው
ማስተዋል አግኝተሽ፤ ቶሎ ብትፈችያቸው
አገር ባደነቀው፤ በቅዱስ ሞያቸው
ላንች ይተርፋሉ፤ እንኳን ለራሳቸው፡፡